# **ምሥራቅን ላከልኝ።**

***

*ከሥርጉተ ሥላሴ*

አረፍ ዓይኔ መጥቶ --- አፈሬ ደርሶልኝ
ዕንባዬን ሊጋራ --- እኔን ሊመስልልኝ፤
ምስራቅን ላከለኝ።
... እያዩሁ ጠገብኩት --- ትዝታ አጎርሰኝ።
ተጎንብሼ ሳምኩት! - ፍጹም ተሳለምኩት!
ጽናት አቀበለኝ ... መንፈሱ ቀረበኝ።
ጉልበቴን፣ ሕይወቴን ....ቅርብ ብዩ አዩሁት ---
ሳሳሁት ... ሳሳሁት .... ሳሳሁት ...
ውስጤን አዩሁበት።
ምርኩዜ ሆነልኝ ---ሚስጢሩ አ<u>ራ</u>ሰኝ፣
ናፍቆት አጎረሰኝ።
ራዕዩን ሰደደ ...
ስንቅ እንዲሆንልኝ፣
ተስፋውን መገበኝ፣ - ትጥቅ እንዲሆንልኝ።
ፀሀይ አስታጠቀኝ - ብርድን እረታልኝ።
.... ጉባኤውም ደምቆ ...
ቅኔውን ቃኜልኝ ...
... ጽጌ አደረሰልኝ።
ማህሌቱም ደርቶ - ሰዓታቱ በርቶ፣
... ዝማሬው ተውቦ ...
ደብር <u>በእያሱ</u> አዩሁትኝ  በርቶ፤
ገላድ ተንተርሶ
ታምራቱ ዳጎሶ።
ዕምነቱ ዳሰሰኝ
ቡራኬው ፈወሰኝ።
ዩልቤ ደረሰ - ነባቢት ቀሰሰ፤
ዓይኔን በዓይኔ አይቶ ካባውን ለበሰ።

<u>ገላድ</u>

- ቅዱስ ወንጌል ላይ የተጠቀሰው ተራራ ጎንደር ደብርበርሃን ሥላሴ በሰተጀርባ ከአጋሙ ሾሎቄ በላይ ይገኛል።
- ዳጉሶ ... ወፍሮ፣ ፋፍቶ ዳብሮ፣ ለምልሞ ....

***<u>ሥጦታ</u>***

እትብቴ ከተቀበረበት ጎንደር ደብረ - ብርሃን ስላሴ ድረስ ሄዳ ጣዕሜን የሀገሬን አፈር ይዛልኝ ለመጣቸው እጅግ ለማከብራት እና ለምወዳት ... ለመንፈሴ ድንቅ ለምስራቅ መንገሻ ይሁንልኝ።

ታህሳስ 3 ቀን 2003  ዓ.ም ቪንተርቱር ሲዊዘርላንድ።